ለመመረቅ መሰናዶ ላይ

# የ 2021 ክፍል

## ዘጠነኛ ክፍል የመጀመሪያ ዓመት፡- 2017–2018

## የ MCPS መመረቂያ መስፈርት በጨረፍታ

የሜሪላንድ ስቴት በአራት ፈርጆች ስኬታማ ክንውን ላይ በመመስረት አንድ ዲፕሎማ ለሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ተመራቂዎች ይፈቅዳል፡ እነዚህም፡- ምዝገባ፣ የኮርስ ክሬዲት፣ የተማሪ ትምህርታዊ አገልግሎት፣ (SSL)፣ እና የሜሪላንድ ምዘና-ግምገማዎች ናቸው። የምዝገባውን ተፈላጊ መስፈርት ለማሟላት ተማሪዎች ከ 8ኛ ክፍል ባሻገር አራት አመታት በሚያመረቃ ሁኔታ መፈፀም አለባቸው። ሌሎች ሁሉም ተፈላጊዎች ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ባጭሩ ተገልፀዋል። እባክዎ ይህንን ድረ-ገጽ MCPS Course Bulletin ይጎብኙ፡- http://coursebulletin.montgomeryschoolsmd.org ወይም የበለጠ መረጃ ለማግኘት የትምህርት ቤትዎን ካውንስለር ያማክሩ።

### የኮርስ ክሬዲቶች

| | |
|---|---|
| እንግሊዘኛ | 4 ክሬዲቶች |
| ኪነ-ጥበባት | 1 ክሬዲት —ከሚመረጡት ኮርሶች ስነጥበብ፣ ዳንስ/ውዝዋዜ፣ ቲአትር፣ እና ሙዚቃ ይህንን መስፈርት ያሟላል (FA)። እነዚህን መስፈርቶች ለማሟላት የተመደቡ ኮርሶች በኮርስ መጽሔት ላይ ተገልጿል። |
| የጤና ትምህርት | 0.5 ክሬዲት |
| የሂሳብ ትምህርት | 4 ክሬዲቶችን 1 የአልጀብራ ትምህርትን ጨምሮ፣ ከሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአልጀብራ መመዘኛ ጋር የሚጣጣም፣ ወይም የአልጀብራ I ቅድመሁኔታ ተከታታይ ተጨማሪ የሂሳብ ኮርሶች፣ እና ከጂኦሜትሪ ይዘት ጋር የሚጣጣም 1 የአልጀብራ ትምህርት።<br>በ 2018 እና ከዚያ በኋላ ለሚመረቁ ተማሪዎች የስቴት አዲስ ተፈላጊ መስፈርት፡-<br>በ 2018 እና ከዚያ በኋላ የሚመረቁ ተማሪዎች በእያንዳንዱ የሁለተኛ ደረጃ ዓመት በሂሳብ ኮርስ መመዝገብ አለባቸው። ይህ ለተማሪዎች መመረቂያ በሂሳብ ከ4 ክሬዲቶች በላይ ሊያስገኝላቸው ይችላል። |
| የሰዉነት ማጎልመሻ ትምህርት | 1 ክሬዲት |
| ሳይንስ | 3 ክሬዲቶች 1 የባዮሎጂ ክሬዲት፣ የተለየ BC፣ እና 1 የፊዚካል ሳይንስ ክሬዲት፣ የተለየ PC፣ መካተት አለባቸው። የበለጠ ዝርዝር ለማግኘት የሳይንስ ዲፓርትመንት የሚሰጣቸውን የኮርስ ዝርዝር ይመልከቱ። |
| የህብረተሰብ ሳይንስ ጥናት | 3 ክሬዲቶችን —1 ዩ.ኤስ ታሪክ ክሬዲት፣ 1 የዓለም ታሪክ ክሬዲት፣ እና 1 ብሔራዊ፣ ስቴት፣ እና የአካባቢ አስተዳደር ክሬዲት አስፈላጊ ነው። |
| የቴክኖሎጂ ትምህርት | 1 ክሬዲት የተመደበ TE። የላቀ ቴክኖሎጂ/Advanced Technology (AT) ኮርሶች የ TE ኮርስ መስፈርትን አያሟሉም ። እነዚህን መስፈርቶች ለማሟላት የተመደቡ ኮርሶች በኮርስ መጽሔት ላይ ተገልጸዋል። |

| በምርጫ የሚወሰዱ ኮርሶች ለምረቃ የሚያስፈልጉትን ተጨማሪ ክሬዲቶች ከሚቀጥሉት ሶስት አማራጮች በአንዱ ማሟላት ይቻላል፡- | ምርጫ 1 | ምርጫ 2 | ምርጫ 3 |
|---|---|---|---|
| | 2 ክሬዲቶች በዓለም አቀፍ ቋንቋ፣ የአሜሪካን የምልክት ቋንቋ የሚያካትት፣<br>እና<br>2.5 ክሬዲቶች ተመርጠው በሚወሰዱ (elective) ኮርሶች | 2 ክሬዲቶች የላቀ/አድቫንስድ ቴክኖሎጂ ትምህርት (AT)<br>እና<br>2.5 ክሬዲቶች ተመርጠው በሚወሰዱ (elective) ኮርሶች | ማጠናቀቅ በስቴት ተቀባይነት ያለው የጥናት ፕሮግራም<br>እና<br>0.5 ክሬዲት ተመርጠው በሚወሰዱ ኮርሶች |

### የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL)

| | |
|---|---|
| የተማሪ የአገልግሎት ትምህርት (SSL) | 75 የአገልግሎት-ትምህርት ሰዓቶች |

### የሜሪላንድ ሁለገብ - አጠቃላይ የምዘና ፕሮግራም
### የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምዘና (MCAP HSA) መስፈርቶች[1,2,3,4]
የ MCAP HSA መስፈርቶች በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) አማካይነት ሊለወጥ ይችላል።

| | |
|---|---|
| አልጀብራ 1 | በአልጀብራ 1 የተገኘ የኮርስ ክሬዲት፣ እና<br>• የአልጀብራ 1 PARCC መውሰድ ወይም አልጀብራ 1 HSA ከ 2016–2017 በፊት፣ ወይም<br>• አልጀብራ 1 በ PARCC ማለፍ |
| HS-MISA<br>የሜሪላንድ የተዋሃደ ሳይንስ ግምገማ | 3 NGSS ሳይንስ ኮርስ፣ እና<br>• HS-MISA 2018–2019 መውሰድ፣ ተማሪው/ዋ በ 2018–2019 በሳይንስ ሦስተኛ ክሬዲት ካገኘ/ች፣ ወይም<br>• ከ 2018–2019 በኋላ HS-MISA ማለፍ |
| እንግሊዝኛ 10 | በእንግሊዝኛ 10 ኮርስ የተገኘ ክሬዲት ወይም ተመጣጣኝ፣ ወይም ESOL 3 ወይም የበለጠ፣ እና<br>• የእንግሊዘኛ ቋንቋ ኪነጥበብ መሰረታዊ ትምህርት 10 PARCC |
| የመንግስት አስተዳደር | በአገር፣ ስቴት፣ እና በአካባቢ አስተዳደር የተገኘ የኮርስ ክሬዲት፣ እና<br>• የመንግስት አስተዳደር በ HSA ማለፍ |

[1] የተተኪ ቴስት—ተማሪዎች በተተኪ ፈተናዎች (AP/IB) የሚፈለገዉን ውጤት የሚያገኙ በዚያ ይዘት መስክ የ MCAP HSA መስፈርትን ያሟላል።

[2] የሚዛወር ክሬዲት—ከሜሪላንድ ውጪ ከህዝብ ትምህርት ቤቶች የሚዛወሩ ተማሪዎች የተወሰኑ የ MCAP HSA ይዘት-አካባቢ ተፈላጊዎችን/መስፈርቶችን በሚዛወር ክሬዲት ለማሟላት ብቃት ሊኖራቸው ይችላል።

[3] ለ HSA እና ለ PARCC ግምገማዎች የተጣመሩ/ተጓዳኝ የፈተና ውጤት አማራጮችይገኛሉ።

[4] መሸጋገሪያ/ድልድይ ፕላን—የ MCAP HSA መመረቂያ መስፈርት ማሟያ አማራጭ መንገድ። በመሸጋገርያ እቅድ አማካይነት፣ መደበኛውን ፈተና ማለፍ የሚያዳግታቸው ተማሪዎች ፕሮጀክቶችን በማከናወን የይዘት ማወቅ/መካን ችሎታቸውን ያረጋግጣሉ/ያሳያሉ።

ለ 2019–2020 የትምህርት ዓመት የሚሠራ የመጨረሻ የተሻሻለው —26 ፌብሯሪ 2019 ነው